# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ
## (2003-2007)

### የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
### ህዳር 2003
### <u>አዲስ አበባ</u>

# ማውጫ


| ተ.ቁ | ርዕስ | ገፅ |
| --- | --- | --- |
| ክፍል አንድ | የመጀመሪያው አምስት ዓመት (1998-2002) የልማት ዕቅድ አፈፃፀም | 1 |
| 1.1 | የልማት ዕቅዱ መነሻዎችና ዓላማ | 2 |
| 1.2 | የልማት ዕቅዱ መሠረታዊ አቅጣጫዎች (Pillar Strategies) | 3 |
| 1.3 | የልማት ዕቅዱ የማክሮ ኢኮኖሚና የዋና ዋና ዘርፎች አፈፃፀም | 4 |
| 1.4 | ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችና የተገኙ ተሞክሮዎች | 8 |
| 1.5 | ማጠቃለያ | 10 |
| ክፍል ሁለት | የቀጣዩ አምስት ዓመት (2003-2007) የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ | 11 |
| 2.1 | የዕቅዱ መነሻዎች | 11 |
| 2.2 | የዕቅዱ ዓላማዎች | 12 |
| 2.3 | የዕቅዱ መሠረታዊ አቅጣጫዎች (Pillar Strategies) | 12 |
| 2.4 | የማክሮ ኢኮኖሚና የዋና ዋና ዘርፎች ግቦች | 24 |
| 2.5 | የአቅም ግንባታና መልካም አስተዳደር ግቦች | 28 |
| 2.6 | የዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት | 29 |
| 2.7 | ማጠቃለያ | 29 |

# ክፍል አንድ

## የመጀመሪያው አምስት ዓመት (1998-2002)
## አገራዊ የልማት ዕቅድ አፈፃፀም

# 1.1 የልማት ዕቅዱ መነሻዎችና ዓላማ

## የልማት ዕቅዱ መነሻዎች

- የመጀመሪያው አምስት ዓመት (1998-2002) የልማት ዕቅድ መነሻዎች ከ1998 በፊት ተፈፃሚ በሆኑ የልማት እንቅስቃሴዎች የተገኙ ውጤቶችና የአገሪቱ ራዕይ ናቸው፡፡

## የልማት ዕቅዱ ዓላማ

- የኢኮኖሚ ዕድገትን በማፋጠንና ዕድገቱ ቀጣይነት እንዲኖረው በማስቻል፣ ሕዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበትና ቢያንስ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት የሚያስችሉ አስተማማኝ የልማት ውጤቶች እንዲኖሩ ማድረግ ነው፡፡

# 1.2 የልማት ዕቅዱ መሠረታዊ አቅጣጫዎች (Strategic Pillars)

## የመጀመሪያው አምስት ዓመት አገራዊ የልማት ዕቅድ መሠረታዊ አቅጣጫዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ሁሉን አቀፍ የማስፈፀም አቅም ግንባታ፣
2. ፈጣን፣ መሠረተ ሰፊና ቀጣይነት ያለውን ኢኮኖሚ ዕድገት ማስፈን፣
3. የሕዝብ ዕድገትና የኢኮኖሚ ዕድገትን የማመጣጠን አቅጣጫ መከተል፣
4. የኢትዮጵያን ሴቶች ሁለንተናዊ አቅም ለመጠቀም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
5. የመሠረተ ልማትን ማጠናከር፣
6. የሰው ኃይል ልማትን አጠናክሮ መቀጠል፣
7. የአደጋ ተጋላጭነት የሚያስከትለውን ሥጋትና አለመረጋጋት መግታትና መቋቋም፣
8. የሥራ ዕድል መፍጠር፣

# የልማት ዕቅዱ ሁለት የዕድገት አማራጮች

- መሠረታዊ የዕድገት አማራጭ (Base Case Scenario)
  - የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች መሠረት ያደረገ፣
  - የ7 በመቶ አማካይ ኢኮኖሚ ዕድገት ግብ ያስቀመጠ፣
- ከፍተኛ የዕድገት አማራጭ (High Case Scenario)
  - አገራዊ ራዕይን መሠረት ያደረገ፣
  - የ10 በመቶ አማካይ የኢኮኖሚ ዕድገት ግብ ያስቀመጠ፣

## 1.3 የልማት ዕቅዱ የማክሮ ኢኮኖሚና የዋናዋና ዘርፎች አፈጻጸም

- ባለፉት አምስት ዓመታት (1998-2002) በሀገራችን ሰፊ መሠረት ያለው ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት ተመዝግቧል፡፡ ይህ አፈፃፀም በማክሮ ኢኮኖሚና በዋና ዋና ዘርፎች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## ሀ.1 አማካይ የኢኮኖሚ ዕድገት ግቦችና የተገኙ ውጤቶች በመቶኛ

| ዘርፍ | አማካይ የኢኮኖሚ ዕድገት ግብ (1998-2002) | | የተደረሰበት አማካይ የኢኮኖሚ ዕድገት (1998-2002) |
|---|---|---|---|
| | መሠረታዊ የዕድገት አማራጭ | ከፍተኛ የዕድገት አማራጭ | |
| ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት | 7.0 | 10.0 | 11.0 |
| ➲ ግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች | 6.0 | 6.4 | 8.0 |
| ➲ ኢንዱስትሪ | 11.0 | 18.0 | 10.0 |
| ➲ አገልግሎቶች | 7.0 | 10.3 | 14.6 |

# ሀ.2 የኢኮኖሚ ዕድገት በመነጨበት ክፍለ ኢኮኖሚ (በመቶኛ)

| ዘርፍ | መነሻ (1997 ) | የዕቅዱ አማካይ ግብ | 1998 | 1999 | 2000 | 2001 | 2002 | የተደረሰበት አማካይ (1998-2002) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት | 12.6 | 7 | 11.5 | 11.8 | 11.2 | 9.9 | 10.4 | 11.0 |
| ➲ ግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች | 13.5 | 6 | 10.9 | 9.4 | 7.5 | 6.4 | 7.6 | 8.36 |
| ➲ኢንዱስትሪ | 9.4 | 11 | 10.2 | 9.5 | 10.0 | 9.9 | 10.6 | 10.04 |
| ➲አገልግሎት | 12.8 | 7 | 13.3 | 15.3 | 16.0 | 14.0 | 13.0 | 14.32 |

## ለ. ዋና ዋና ዘርፎች ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ያላቸው ድርሻ (በመቶኛ)

| ዘርፍ | መነሻ (በ1997) | የዕቅዱ የኢኮኖሚ ዕድገት አማካይ ግብ (1998-2002) | | በ2002 የተደረሰበት |
|---|---|---|---|---|
| | | መሠረታዊ የዕድገት አማራጭ | ከፍተኛ የዕድገት አማራጭ | |
| ➲ግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች | 47.4 | 43.9 | 39.0 | 41.55 |
| ➲ኢንዱስትሪ | 13.6 | 16.5 | 20.0 | 12.87 |
| ➲አገልግሎት | 39.0 | 39.6 | 41.0 | 45.58 |
| ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት | 100 | 100 | 100 | 100 |

## ሐ. ጠቅላላ ፍጆታ፣ ኢንቨስትመንትና  የሀብት ክፍተት ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ ድርሻ (በመቶኛ)

| ዘርፍ | መነሻ (1997 ) | መድረሻ (2002) |
|---|---|---|
| ጠቅላላ የፍጆታ ወጪ | 94.1 | 90.6 |
| ጠቅላላ ኢንቨስትመንት | 23.8 | 23.9 |
| ጠቅላላ የወጪ ንግድ | 15.1 | 13.6 |
| ጠቅላላ የገቢ ንግድ | 35.5 | 28.1 |
| የሀብት ክፍተት | (20.4) | (14.5) |
| ጠ/የአገር ውስጥ ቁጠባ ከጠ/የአገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በመቶኛ | 5.9 | 9.4 |
| ከአጠቃላይ ድህነት መሥመር በታች የሚኖረው ሕዝብ ብዛት በመቶኛ | 39 | 29.2 ግምት |
| ከምግብ ድህነት መስመር በታች የሚኖር ሕዝብ ብዛት በመቶኛ | 38 | 28.2 ግምት |

# ሠንጠረዥ 1.3.2 የዋና ዋና ዘርፎች አፈጻጸም

| ዘርፍ | መነሻ (1997) | መድረሻ (2002) |
| --- | --- | --- |
| **ግብርና** | | |
| የዋና ዋና ሰብሎች ምርት (በሚሊዮን ቶን) | 11.9 | 18.08 |
| የዋና ዋና ሰብሎች ምርታማነት (ኩ/ሄር) | 13.1 | 17 |
| **ትምህርት** | | |
| የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ንጥር ተሳትፎ በመቶኛ | 68.5 | 87.9 |
| የሥርዓተ ፆታ የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ ጥምርታ | 0.87 | 0.93 |
| የተማሪና መፅሀፍት ጥመርታ | 2:1 | 1.25:1 |

# ሠንጠረዥ 1.3.2 የዋና ዋና ዘርፎች አፈጻጸም

| ዘርፍ | መነሻ (1997) | መድረሻ (2002) |
|---|---|---|
| ጤና | | |
| የጤና አገልግሎት ሽፋን በመቶኛ | 30 | 89 |
| የእናቶች ሞት መጣኔ (በ100000) | 871 | 590 |
| ከ5 ዓመት በታች የሕፃናት ሞት መጣኔ (በ1000) | 123 | 101 |
| በሰለጠነ ባለሙያ የታገዙ ወላዶች መጣኔ በመቶኛ | 9 | 25 |
| የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችና ህዝብ ጥምርታ | 1፡25000 | 1፡2500 |

## ሠንጠረዥ 1.3.2 የዋና ዋና ዘርፎች አፈጻጸም...የቀጠለ

| ዘርፍ | መነሻ (1997) | መድረሻ (2002) |
|---|---|---|
| መሠረተ ልማት | | |
| ሀ. ውሀ | | |
| የንፁህ መጠጥ ውሀ ሽፋን (በከተማ) በ0.5 ኪ.ሜ ርቀት | 80 | 91.5 |
| የንፁህ መጠጥ ውሀ ሽፋን (በገጠር) በ1.5 ኪ.ሜ ርቀት | 35 | 65.8 |
| አጠቃላይ የንፁህ መጠጥ ውሀ ሽፋን | 36 | 68.5 |
| ለ. መንገድ | | |
| ጠቅላላ የመንገድ ርዝመት በሺህ ኪሎ ሜትር (የወረዳ መንገዶችን ሳይጨምር) | 36.4 | 48.8 |
| በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝ መንገድ (በመቶኛ) | 64 | 81 |
| በክረምትና በበጋ ወደሚያስኬዱ መንገዶች ለመድረስ የሚወስደው ጊዜ (በሰዓት) | 5.7 | 3.7 |

## ሠንጠረዥ 1.3.2 የዋና ዋና ዘርፎች አፈጻጸም...የቀጠለ

| ዘርፍ | መነሻ (1997) | መድረሻ (2002) |
|---|---|---|
| ሐ. መብራት | | |
| የመብራት አገልግሎት ሽፋን (በመቶኛ) | 16 | 41 |
| የመብራት አገልግሎት ተጠቃሚ ከተሞችና የገጠር መንደሮች (በቁጥር) | 648 | 5163 |
| የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት (በሜጋ ዋት) | 714 | 2000 |

# ሠንጠረዥ 1.3.2 የዋና ዋና ዘርፎች አፈጻጸም...የቀጠለ

| ዘርፍ | መነሻ (1997) | መድረሻ (2002) |
|---|---|---|
| **መ. ቴሌኮሚኒኬሽን** | | |
| የቴሌፎን አገልግሎት ሽፋን (በ5 ኪ.ሜ ክልል) (በመቶኛ) | 13 | 62.14 |
| የቴሌፎን አገልግሎት የሚያገኙ ቀበሌዎች ቁጥር | 3000 | 13000 |
| የሞባይል ስልክ ተጠቃሚዎች (በሚሊዮን) | 0.56 | 6.52 |
| የመደበኛ ስልክ ተጠቃሚዎች ቁጥር (በሚሊዮን) | 0.62 | 1.00 |
| የኢንተርኔት ስልክ ተጠቃሚዎች ቁጥር (በሚሊዮን) | 0.02 | 0.187 |

# የኢንዱስትሪ ልማት

- በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞች ልማት ዘርፍ፣
- በጨርቃጨርቅና አልባሳት፣
- በቆዳና ቆዳ ውጤቶች ረገድ፣
- የስኳር ኢንዱስትሪ ልማትን በተመለከተ፣
- የሲማንቶ ኢንዱስትሪ ልማትን በተመለከተ፣
- የብረታ ብረትና ኢንጅንሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት፣
- በኬሚካል ኢንዱስትሪ ልማት ረገድ፣
- በፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ በኩል፣
- የአግሮ ኘሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ልማትን፣

በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

## 1.3.3 አቅም ግንባታና መልካም አስተዳደር

- የህዝብ ተሳትፎን በማስፋትና በማጠናከር በርካታ የልማትና የዲሞክራሲ ሥርት ግንባታ ሥራዎች ተከናውነዋል፣

- ባልተማከለ የወረዳ አስተዳደር ዙሪያ በተለይ የገጠር የወረዳዎችን አቅም ለማጠናከር የወረዳና የቀበሌ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን የማሻሻል፣ አስፈላጊውን የሰው ኃይል የማሟላት ሥራዎች በሠፊው ተሠርተዋል፣

- በ1999 ዓ.ም ተግባራዊ መሆን በጀመረው የከተሞች የመልካም አስተዳደር ፕሮግራም አማካይነት በመሬት፣ በፋይናንስና በከተማ ፕላን ዙሪያ ግልፅነትንና ተጠያቂነትን የሚያሰፍኑ እንዲሁም ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ የሕግ ማዕቀፎች፣ የአደረጃጀትና የአሰራር ሥርዓቶች ተግባራዊ ሆነዋል፣

- ሙስናን በመከላከል ረገድ ባለፉት ዓመታት በዜጋውም ሆነ በሰራተኛው ውስጥ ሙስናንና አድሎን የመቃወም ጅምር መታየቱ፣ ሙሰኞችን ማጋለጥና ከሶ ማስቀጣት እየጨመረ መምጣቱ፣ በዕቅዱ ዘመን የተመዘገቡ ስኬቶች ናቸው፡፡

## 1.4 ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችና የተገኙ ተሞክሮዎች

### 1.4.1 ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች

- በአገሪቱ ታሪክ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ የዋጋ ንረት መከሰትና በክፍያ ሚዛን ላይ ጫና ማሳደሩ ዋና ፈታኝ ጉዳይ የነበረ ሲሆን መንግሥት በወሰዳቸው አስተዳደራዊና የፖሊሲ እርምጃዎች አጠቃላይ የዋጋ ግሽበትን በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስ ተችሏል፡፡

- የልማት ዕቅዱን ከማስፈጸም አኳያ የአገር ውስጥ የገቢ አሰባሰብ ከፍተኛ ለውጥ የታየበት ቢሆንም የሚጠበቀውን ያህል አለመሆኑ ሌላው ፈታኝ ጉዳይ ሲሆን በዚህ ዙሪያ መንግሥት ሥርነቀል የማሻሻያ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡

- የሀገር ውስጥ የቁጠባ መጠን አነስተኛ መሆን ለኢኮኖሚው ዕድገት የሚፈልገውን የኢንቨስትመንትን መጠን ለመደገፍ የሚያስችል ሀብት ማሰባሰብ አላስቻለም በመሆኑም በቀጣይ የሀገር ውስጥ ቁጠባን ማሳደግ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ይሆናል፡፡

# 1.4 ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችና የተገኙ ተሞክሮዎች.. የቀጠለ

## 1.4.1 ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች...

- ባለፉት ዓመታት የዝናብ ስርጭቱ በአብዛኛው መልካም የነበረ ቢሆንም በአንዳንድ ዝናብ አጠር አካባቢዎች በአንጻራዊ ሁኔታ የክረምት ወቅት ዝናብ ዘግይቶ የመጀመርና ፈጥኖ የመውጣት እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች የበልግ ዝናብ መዛባት ተከስቷል፡፡

- ይህም መንግስት በአነስተኛ፣ በመካከለኛና በትላልቅ መስኖ ልማት ዙሪያ የሚያደርገውን ጥረት አጠናክሮ እንዲቀጥል አመላካች ሆኗል፣

## 1.4 ፈታኝ ሁኔታዎችና የተገኙ ተሞክሮዎች....የቀጠለ

### 1.4.2 የተገኙ ተሞክሮዎች

- ኢኮኖሚውን በመምራትና በማስተዳደር ሂደት ልማታዊ ባለሀበቶችን፣ ህዝቡን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የማስተባበርና የማቀናጀት ሰፊ ተሞክሮ መገኘቱ፣

- የአገር ውስጥ ሀብትን በማሰባሰብና በአገር ውስጥ አቅም ሰፋፊ የልማት ሥራዎችን የማከናወን ሰፊ ልምድ መገኘቱ፣

- የመልካም አስተዳደር ፓኬጅን በመተግበር የሰው ኃይል ግንባታ፣ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፣ የህዝብ ተሳትፎን የማስፋትና የማጠናከር፣ የተቀናጀ የተቋም አቅም ግንባታ፣ ግልፅነትና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ ልምድ መገኘቱ፣

- የግብርናውን ዘርፍ በምርትና በምርታማነት በሚፈለገው መጠን ለማሳደግ የሚያስችል ሞዴል ገበሬዎችን በማፍራት መልካም ተሞክሮ መገኘቱ፣

- በኢንዱስትሪው ልማት ዘርፍ በኩል በተለይም በማኒፋክቸሪንግ ዘርፍ የሚፈለገውን ያህል ዕድገት ያልታየ ሲሆን ከዚሁ ሂደት በቀጣይ የዘርፉን ዕድገት ለማበረታታት ትምህርት መወሰዱ፣

- በማህበራዊ ልማት ዘርፍ አገልግሎቶችን በማስፋት ከፍተኛ ውጤት ቢመዘገብም ጥራቱ መሻሻል እንዳለበት የሚያሳዩ ሰፊ ተሞክሮዎች መገኘታቸው፣

## 1.5 ማጠቃለያ

- ባለፉት አምስት ዓመታት አገራችን ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን በማረጋገጥ፤ ማህበራዊ ልማትን በማፋጠን እና ዲሞክራሲያዊና ልማታዊ መንግሥትን እውን በማድረግ ረገድ በታሪካችን ታይቶ የማይታወቅ ከፍተኛ ለውጥና ድል አስመዝግባለች፡፡ በዚህ ስኬታማ ሂደት ፈታኝ ሁኔታዎችን በመወጣት ለቀጣይ የልማት ሥራዎቻችን ተጨማሪ ጉልበት የሚሆኑ ትምህርቶችን ቀስማለች፤

- ባለፉት አምስት ዓመታት በአገራችን የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት በኢትዮጵያ የዕድገት ደረጃ ላይ ባሉ አገሮች ያልታየና ያልተደረሰበት ነው፤

- የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት ማንኛውም ዓይነት ሳይሆን ፈጣንና ዘላቂነት ያለው ነው፡፡

## 1.5 ማጠቃለያ.....የቀጠለ

- የተመዘገበው ዕድገት ፈጣንና ዘላቂነት ያለው መሆኑ ብቻ ሳይሆን መሠረተ ሰፊና ሕዝቡን በየደረጃው ተጠቃሚ ያደረገ ነው፤

- ይህ የኢኮኖሚ ዕድገት ወደፊት ዘላቂ ሆኖ ከቀጠለ በአጭር ጊዜ ውስጥ የምግብ ዋስትናችን ለማረጋገጥና በቀጣይም ሩቅ በማይባል ጊዜ ውስጥ ድህነትን ለማስወገድ እንደምንችል ጥርጥር የለውም፤

- በመሆኑም ባለፉት ዓመታት ሥራ ላይ በዋሉ የልማት ዕቅዶች ከተመዘገቡ ውጤቶች የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች በቀጣዩ የአምስት ዓመት አገራዊ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተወስደው በስፋት ሥራ ላይ ይውላሉ፡፡ በዚህ ሂደትም ቢያንስ እስካሁን የተደረሰበትን የኢኮኖሚ ዕድገት በማስጠበቅ በተቀናጀና በተባበረ አገራዊ የልማት ክንድ ካለፉት ዓመታት በእጅጉ የላቀ ውጤት እናስመዘግባለን፤

# ክፍል ሁለት

## የቀጣዩ አምስት ዓመት (2003-2007) የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ

## 2.1 የዕቅዱ መነሻዎች

- የቀጣዩ የአምስት ዓመት (2003-2007) ዕቅድ መነሻዎች የአገሪቱ ራዕይ፣ በአለፉት ዓመታት ተፈፃሚ በሆኑ ዕቅዶች የተመዘገቡ ውጤቶችና በአፈፃጸም ሂደት የተገኙ ተሞክሮዎች ናቸው፡፡

- የአገሪቱ ራዕይ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2012-2015 በህዝብ ተሳትፎና በህዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት፣ ማህበራዊ ፍትህ የነገሰባት፣ ከድህነት ተላቅቃ መካከለኛ ገቢ ያላት ኢትዮጵያን ዕውን ማድረግ ነው፡፡

- በኢኮኖሚው መስክ የኢትዮጵያ ራዕይ፡-
  - በከፍተኛ የቴክኖሎጂና ምርታማነት ደረጃ ላይ የደረሰ ዘመናዊ ግብርናና በኢኮኖሚው ውስጥ የመሪነት ሚና መጫወት የሚችልበት ደረጃ ላይ የደረሰ ኢንዱስትሪ ያለው ኢኮኖሚ የገነባች፣
  - ፍትሀዊነት የተረጋገጠበት ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚ ልማት ያላት፣
  - የዜጎች የነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ገቢ መካከለኛ ዕድገት ያላቸው አገሮች በደረሱበት ደረጃ ላይ የደረሰባት አገር መሆን ነው፡፡

- የዕቅዱ መሪ አጀንዳ ባለፉት ዓመታት ተፈፃሚ ከሆኑ የልማት ዕቅዶች የተገኘውን መሠረተ ሰፊ፣ ፈጣን፣ ቀጣይና ፍትሀዊ የኢኮኖሚ ዕድገት አጠናክሮ በመቀጠል ድህነትን በሂደት ማስወገድ ነው፡፡

## 2.2 የዕቅዱ ዓላማዎች

- አጠቃላይ ኢኮኖሚው በየዓመቱ ቢያንስ በአማካይ 11 በመቶ ዕድገትን በማስመዝገብ በኢኮኖሚያችን መታየት የጀመሩትን ማነቆዎች በማስወገድና በማቃለል የሚሌኒየም ልማት ግቦችን ማሳካት፣

- የትምህርትና ጤና አገልግሎት ሽፋንን በመጨመርና ጥራቱን በማረጋገጥ ላይ የተመሠረተ ማህበራዊ ልማት በማካሄድ የሚሌኒየም ልማት ማህበራዊ ግቦችን ማሳካት፣

- የተረጋጋ፣ ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ መንግስትን በመፍጠርና በማጠናከር ለቀጣይ የአገር ግንባታ ሥራ ምቹ መደላድል መፍጠር፣

- ከላይ የተገለፁትን ዋና ዋና ዓላማዎች በተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ውስጥ በመፈፀም የልማቱን ቀጣይነት ማረጋገጥ፣

# 2.3 የዕቅዱ መሠረታዊ አቅጣጫዎች (Pillar Strategies)

2.3.1 ፈጣን፣ ቀጣይና ፍትሀዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ፣

2.3.2 የግብርና ዘርፍ ዋና የዕድገት ምንጭ ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ፣

2.3.3 የኢንዱስትሪው ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ቁልፍ ሚና እንዲጫዎት ማስቻል፣

2.3.4 የመሠረተ ልማትን ማስፋፋትና ጥራትን ማረጋገጥ፣

2.3.5 የማህበራዊ ልማትን ማፋጠንና ጥራትን ማረጋገጥ፣

2.3.6 አቅም ግንባታንና መልካም አስተዳደርን ማሳደግ እና

2.3.7 የሴቶችንና የወጣቶችን ብቃትና ተጠቃሚነት ማሳደግ፣

## 2.3.1 ፈጣን፣ ቀጣይና ፍትሀዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ፣

- በአለፉት 5 ዓመታት የተመዘገበውን የኢኮኖሚ ዕድገት በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በዘላቂነት አጠናክሮ መቀጠልና ህዝቡን በየደረጃው ተጠቃሚ ማድረግ፣
- ዕድገትን ለማፋጠን በሚያስችሉ የኢኮኖሚ መሠረተ ልማትና የማህበራዊ ልማት ዘርፎች ላይ ከአሁን በፊት የተሰጠውን ትኩረት አጠናክሮ መቀጠል፣
- እንዳለፉት ዓመታት የግብርናውን ምርታማነት በማሳደግና ዘላቂነትን በማረጋገጥ ግብርና በቀጣዩ አምስት ዓመት የኢኮኖሚ ዕድገት ዋነኛ ምንጭ ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ፣
- የወጪ ንግድ መር ኢንዱስትሪ ልማትን መሠረት በማድረግ የኢንዱስትሪው ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ተገቢውን ሚና እንዲጫወት የሚያስችል ምቹ መደላድል መፍጠር፣
- ውድድርን መሠረት በማድረግ ገቢ ንግድን ለሚተኩ ኢንዱስትሪዎች በቂ ትኩረት በመስጠት ኢንዱስትሪ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች በላቀ ፍጥነት እንዲያድግና ለቀጣዩ የልማት ምዕራፍ መሠረት እንዲሆን ማድረግ፣
- ፈጣን፣ ቀጣይና ፍትሀዊ የኢኮኖሚ ዕድገትን በማስፈን የሥራ ዕድልን ማስፋፋትና ድህነትን በሂደት ማስወገድ፣

# የኢኮኖሚ ዕድገት አማራጮች

ፈጣን፣ ዘላቂና ፍትሀዊ ዕድገት ለማረጋገጥ በቀጣዩ አምስት ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ዘመን ሁለት የኢኮኖሚ ዕድገት አማራጮች ታይተዋል፡፡ እነዚህም መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዕድገት አማራጭ (Base case scenario) እና ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት አማራጭ (High case scenario) ናቸው፡፡

- በመሠረታዊው የኢኮኖሚ ዕድገት አማራጭ (Base case scenario) ኢኮኖሚው ላለፉት አምስት ዓመታት በየዓመቱ በአማካይ ያስመዘገበውን የ11 በመቶ ዕድገት ቀጣይነት ማረጋገጥ፣

- በከፍተኛው የኢኮኖሚ ዕድገት አማራጭ (High case scenario) የግብርና ምርትንና አጠቃላይ ኢኮኖሚውን በ2002 ከነበሩበት በ2007 ዕጥፍ ማድረግና ይህንኑ ለማሳካት ኢኮኖሚውን በየዓመቱ በአማካይ በ14.9 በመቶ ማሳደግ፣ የኢንዱስትሪውን ዕድገት በማፋጠን ዘርፉ በኢኮኖሚው ውስጥ የመሪነት ሚናውን ሊረከብ የሚችልባቸውን ሥራዎች ማጠናቀቅ፣

- ሁለቱ አማራጮች ከዚህ ቀጥሎ በሠንጠረዥ 2.3.1.1 እና በሠንጠረዥ 2.3.1.2 ቀርበዋል፣

## ሠንጠረዥ 2.3.1.1 ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ዕድገት በመነጨበት ክፍለ ኢኮኖሚ በመቶኛ

| ዘርፍ | መነሻ (2002 ) | አማካይ ግብ (2003-2007) | |
|---|---|---|---|
| | | መሠረታዊ የዕድገት አማራጭ | ከፍተኛ የዕድገት አማራጭ |
| ➲ ግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች | 7.60 | 8.58 | 14.9 |
| ➲ ኢንዱስትሪ | 10.60 | 20.00 | 21.4 |
| ➲ አገልግሎት | 13.00 | 10.60 | 12.8 |
| ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት | 10.40 | 11.20 | 14.9 |

## ሠንጠረዥ 2.3.1.2 ዋና ዋና ዘርፎች ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት የሚኖራቸው ድርሻ በመቶኛ

| ዘርፍ | መነሻ (2002 ) | መድረሻ በ2007) | |
|---|---|---|---|
| | | መሠረታዊ የዕድገት አማራጭ | ከፍተኛ የዕድገት አማራጭ |
| ➲ ግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች | 41.0 | 36.88 | 41.0 |
| ➲ ኢንዱስትሪ | 13.0 | 18.78 | 16.9 |
| ➲ አገልግሎት | 46.0 | 44.34 | 42.1 |
| ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት | 100 | 100 | 100 |

## 2.3.1.3 ጠቅላላ ፍጆታ፣ ኢንቨስትመንትና የሀብት ክፍተት ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ የሚኖራቸው ድርሻ (በመቶኛ)

| ዘርፍ | መነሻ (በ2002 ) | አማካይ (በ2003-2007) | |
|---|---|---|---|
| | | መሠረታዊ የዕድገት አማራጭ | ከፍተኛ የዕድገት አማራጭ |
| ጠቅላላ የፍጆታ ወጪ | **94.5** | **88.1** | **88.9** |
| ጠቅላላ ኢንቨስትመንት | **23.7** | **27.0** | **22.0** |
| ጠቅላላ የወጪ ንግድ | **13.6** | **19.4** | **19.7** |
| ጠቅላላ የገቢ ንግድ | **28.1** | **35.0** | **30.5** |
| የሀብት ክፍተት | **(19.3)** | **(15.6)** | **(10.8)** |
| ጠቅላላ የአገር ውስጥ ቁጠባ | **5.5** | **11.9** | **11.1** |
| ከአጠቃላይ ድህነት መስመር በታች የሚኖረው ህዝብ በመቶኛ | 29.2 ግምት | 22.2 ግምት | - |
| ከአጠቃላይ ድህነት መስመር በታች የሚኖረው ህዝብ በመቶኛ | 28.2 ግምት | 21.2 ግምት | - |

## 2.3.2 የግብርና ዘርፍ ዋና የዕድገት ምንጭ ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ፣

- የግብርና ልማት ስትራቴጂ አቅጣጫዎችን በመከተልና በአለፉት ዓመታት በዘርፉ የተገኙ ተሞክሮዎችን መሠረት በማድረግ የአርሶ/አርብቶ አደሩን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ የተጀመረውን ገበያ ተኮርና የተሻለ ምርት ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የማምረት ሂደት አጠናክሮ መቀጠል፡-
  - ምርጥ አርሶ አደሮች የሚጠቀሙበትን ቴክኖሎጂ ወደ ሁሉም አርሶ አደሮች በማስፋፋት የአነስተኛ አርሶ አደሩን ምርታማነት ወደ ምርጥ አርሶ አደሮች ምርታማነት ደረጃ የተጠጋ እንዲሆን ማድረግና ምርትና ምርታማነትን የበለጠ ለማሳደግ በሚያስችል ሁኔታ አርሶ አደሩን የሚደግፍ የመንግስት መዋቅር ቀጣይነት ማጠናከር፣ አርሶ አደሩ ያለው ለልማት መነሳሳት የተደራጀና ውጤታማ እንዲሆን የማድረግ፣
  - አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በተከታታይ እንዲፈተሹና ፈጥነው ለአርሶ አደሩ/አርብቶ አደሩ እንዲደርሱ ይደረጋል፤
  - የተፈጥሮ ሀብትን በመጠበቅ የመስኖ ልማትን በማስፋፋት የግብርናን ዕድገት ማፋጠንና ቀጣይነቱን ማረጋገጥ ዋና የትኩረት አቅጣጫ ሲሆን የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤ በማካሄድ በዋነኛነት የአርሶ አደሩንና የደጋፊ የመንግስት መዋቅሮችን አቅም በመጠቀምና በቀጣይነትም በመገንባት የሚፈፀም ይሆናል፡፡
  - አርሶ አደሩን የተሻለ ዋጋ ወዳላቸው ምርቶች በማሸጋገር ከምርቱ የሚያገኘው ገቢ እንዲያድግ ለማድረግ መለስተኛ ዋጋ ያላቸውን ምርቶች ከማምረት ደረጃ በደረጃ የተሻለ ዋጋ ወዳላቸው ምርቶች እንዲሸጋገር ማድረግ፣ ይህንንም ከአካባቢ ስፔሻላይዜሽን ጋር በማስተሳሰርና ከአመቺ የገበያና የመሠረተ ልማት መስፋፋት ጋር በማያያዝ ደረጃ በደረጃ ተፈፃሚ ማድረግ፡፡

## 2.3.2 የግብርና ዘርፍ ዋና የዕድገት ምንጭ.....የቀጠለ፣

- በግብርናው ዘርፍ የግል ባለሀብቶችን የኢንቨስትመንት ተሳትፎ ማበረታታትና ለሰፋፊ እርሻ አልሚዎች በተሻለ ሁኔታ ድጋፍ ማድረግ፣

  - በውስን መሬት ሰፊ ጉልበትን በመጠቀም ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ምርቶች በማምረት ላይ የተመሠረተውና በዋናነት በሆርቲካልቸር ምርት ላይ የሚያተኩረው የግብርና ልማት ዘርፍ በዋናነት በደጋማው አካባቢና ለዋና ዋና ከተሞች ቅርበት ባላቸው አካባቢዎች ከአርሶ አደሩ የምርት እንቅስቃሴ ጋር እየተቀናጀ የሚቀጥልና ተፈፃሚ የሚደረግ ይሆናል።

  - ለግብርና የሚያመቹ ሰፋፊ መሬቶች ባሉባቸው አካባቢዎች መሰረተ ልማት እየተስፋፋ በመምጣቱ ለልማቱ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል። እነዚህን ምቹ ሁኔታዎች በመጠቀም በግብርና ዘርፍ በግሉ ኢንቬስትመንት ድርሻና ተሳትፎ ላይ እመርታ ማስመዝገብ አንድ መሠረታዊ አቅጣጫ ይሆናል። ሰፋፊ መሬቶችንና ውስን ጉልበትን በመጠቀም በቆላማ አካባቢዎች ሰፋፊ እርሻዎችን ለሚያለሙ የግል ባለሀብቶች አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል።

## 2.3.2 የግብርና ዘርፍ ዋና የዕድገት ምንጭ.....የቀጠለ፣

- ከፍተኛ የመልማት አቅም ላላቸው አካባቢዎች ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ገበያው በሚፈልጋቸውና ሀገሪቱ የተሻለ የገበያ ዋጋ ልታገኝባቸው በምትችልባቸው የምርት አይነቶች ላይ በማተኮር አርሶ አደሮችና የግል ባለሀብቶች እንዲያመርቱ ማበረታታት፣
- የግብርና ምርቶችን የግብይት ሥርዓት በተዋናዮችና በባለድርሻ አካላት የነቃና የተደራጀ ተሳትፎ ከምርት እስከ ወጭ ንግድ ጫፍ ወጥና በተሟላ አኳኋን በመገንባት ለግብርና ምርት ግብይት አመቺ ሁኔታ መፍጠርና ዘመናዊ የግብይት ስርዓቱ የበለጠ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ፣
- በዘርፉ የሚደረጉ ልማት ጥረቶችን ለማገዝ የተጀመሩትን የተለያዩ የመንግስት ኢንቨስትመንትና አገልግሎቶች የማስፋፋት ስራ አጠናክሮ መቀጠል፣
- ግብርና በየዓመቱ በፍጥነት እንዲያድግ በማድረግ፡-
    - የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣
    - የዋጋ ግሽበት ግፊትን የማስወገድ ወሳኝ ድርሻ እንዲጫወት ማድረግ፣
    - የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ለመቅረፍ ከፍተኛ ድርሻ እንዲያበረክት ማድረግ፣
    - መካከለኛ ገቢ ያላት አገር የመፍጠር ራዕይን ለማሳካት ድርሻውን እንዲወጣ ማድረግ፣
    - ለኢንዱስትሪ ልማት የበኩሉን ድርሻ እንዲጫወት ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

## 3.3 የኢንዱስትሪው ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ቁልፍ ሚና እንዲጫዎት ምቹ መደላድል መፍጠር፣

- በኢንዱስትሪ መስክ ከማንኛውም ዘርፍ የፈጠነና የተሻለ ልማት በማረጋገጥ፡-
  - ኢንዱስትሪው ደረጃ በደረጃ የቀጣይ የሀገሪቱ ልማት መሠረት የሚሆንበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
  - ኢንዱስትሪው የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ለማቃለል የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ማድረግ፣
  - ኢንዱስትሪው ለግብርና ቀጣይ ልማት የበኩሉን ድርሻ እንዲያበረክት ማድረግ፣
  - ኢንዱስትሪው ሰፊ የሥራ ዕድል የሚፈጥርበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ የላቀ ትኩረት በመስጠት የተለያዩ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ማድረግ፣
  - በኢንዱስትሪው ዘርፍ በሁለት ንዑስ ዘርፎች ላይ ትኩረት ይደረጋል፡- 1ኛ/ ለአነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎች 2ኛ/ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለመካከለኛና ለከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ትኩረት ይሰጣል፡፡

- ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት መስፋፋትና መጠናከር ትኩረት በመስጠት፡-
  - የሥራ ዕድሎች እንዲፈጠሩ ማድረግ፣
  - የከተሞችን ዕድገት ማፋጠን፣
  - ለግብርና ልማት የቅርብ ድጋፍ መስጠት፣
  - አዳዲስ ባለሀብቶች እንዲፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣

## 2.3.3 የኢንዱስትሪው ዘርፍ ...የቀጠለ፣

- ለመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የቴክኖሎጂ እድገትን በማረጋገጥ፡-
  - የአገራችን ኢኮኖሚ ተወዳዳሪነት እንዲገጎለብት ማድረግ፣
  - የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ ማድረግ፣
  - ለግብርና ዘርፍ ዕድገት አመቺ ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረግ፣
- ዘርፉ እንዳለፈው ጊዜ ሁሉ በኤክስፖርት ኢንዱስትሪ የሚመራና ለውጭ ምንዛሪ ማነቆ መቀረፍ፣ ለፈጣን የቴክኖሎጂ ሽግግር ድርሻውን የሚወጣ እንዲሆን ማድረግ፣
- ገቢ ምርቶችን የሚተኩ ኢንዱስትሪዎችም የውጭ ምንዛሪ እጥረታችንን በማቃለል ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ስላላቸውና ለቀልጣፋ የኢንዱስትሪ ዕድገት መሠረት የሚሆኑ በመሆናቸው ከመቼውም ጊዜ የላቀ ትኩረት በመስጠት እንዲስፋፉ ማድረግ፣

## 2.3.3 የኢንዱስትሪው ዘርፍ ...የቀጠለ፤

- ለዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል በበቂ መጠንና ጥራት ለማቅረብ የከፍተኛ ትምህርትና የቴክኒክና ሞያ ሥልጠና ተቋማት በኢንዱስትሪ ልማት የተቃኘና ይህንኑ እንደሚያገለግል አድርጎ መፈፀም፤ የውጭ ቴክኒካዊ ድጋፍና የውጭ ኢንቨስትመንት በዋናነት የሥራ አመራር ጥበብ ለውጥ ዕድሎችን የቴክኖሎጂ ሽግግርና የሙያተኛ አቅም በሚፈጥር መልክ መጠቀም፤

- የተማረው ወጣት አነስተኛና ጥቃቅን ተቋሞችን በማደራጀት የራሱን ሥራ እንዲፈጥር በሂደትም የአገሪቱን የኢንዱስትሪ ልማት የሚያንቀሳቅሱ ኢንዱስትሪያሊስቶች እንዲፈጥር የማድረግ አቅጣጫ መከተል፤

- የኢንተርፕርኔርሽፕ አስተሳሰብና ዕውቀት እንዲዳብር፤ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዲጠናከር፤ የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ማዕከላት የአነስተኛና የጥቃቅን ተቋሞችን ልማት በቴክኖሎጂ ሽግግር የሚደግፉና የተሟላ የቴክኖሎጂ ድጋፍ እንዲሰጡ ማስቻል፤

## 2.3.3 የኢንዱስትሪው ዘርፍ ...የቀጠለ፣

- ፍላጎቱና ብቃቱ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶችን በብዛት ለመፍጠርና ጥረታቸውን በውጭ ባለሀብቶች ተሣትፎ በማጎልበት ለኢንዱስትሪ ልማት ምቹ ሁኔታን መፍጠር፣

- የኢንቨስትመንት ወጪን ለመቀነስ፣ ኢንዱስትሪዎች ተሰባስበው የሚደጋገፉበት ሁኔታን ለመፍጠር ስብስቦቹ የሚቋቋሙባቸው የኢንዱስትሪ መንደሮችና ቀጠናዎችን ማደራጀት፣
  - ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር በመቀናጀት በፌዴራል መንግስት አማካኝነት የተሟላ የሥራ ቦታ፣ መሠረተ ልማትና አስተዳደራዊ አገልግሎት ያላቸው የኢንዱስትሪ መንደሮችን በተመረጡ አካባቢዎች መገንባት፣
  - በተጠናና ውጤታማ በሆነ አግባብ መለስተኛ የኢንዱስትሪ መንደሮች/የኢንዱስትሪ ቀጣናዎች በክልሎች እንዲቋቋሙ መደገፍ፣
  - በዚህ አኳኋን የተለያየ አገራዊና ክልላዊ ፋይዳ ያላቸው የዕድገት ማዕከላት እንዲፈጠሩና ከአካባቢው ገጠር ጋር ተመጋግበው የልማት ቀጣናዎች እየጐለበቱ እንዲሄዱ ማድረግ፣
  - ሌላ አጥጋቢ አማራጭ በማይኖርበት ወቅት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ብቻቸውንም ሆነ ከግል ባለሀብቶች ጋር በመቀናጀት የተመረጡ ኢንቨስትመንቶችን እንዲያከናውኑ ይደረጋል፣

## 2.3.4 የመሠረተ ልማት ማስፋፋትና ጥራትን ማረጋገጥ፣

- በመሠረተ-ልማት መስፋፋት መስክ ያጋጠሙ ዋነኛ ችግሮችን በመቅረፍ በዘርፉ የሚከናወነውን ኢንቨስትመንት በከፍተኛ መጠን መጨመር፣
- የአገር ውስጥ ቁጠባን ማሻሻልና ለመሠረተ ልማት መስፋፋት ሥራ የሚያስፈልጉ ከውጭ የሚገቡ ቁሳቁሶችና አገልግሎቶች በተቻለ መጠን በአገር ውስጥ የሚመረቱበትን ወይም የሚቀርቡበትን ሁኔታ መፍጠር እና በውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ላይ የሚፈጥረውን ጫና በከፍተኛ መጠን መቀነስ፣
- የኢኮኖሚ ዕድገቱ እንዲፋጠን የሚፈለጉ የትራንስፖርትና መገናኛ፣ የኃይል አቅርቦትን በጥራትና በተወዳዳሪ ዋጋ ማቅረብ፣
- ለመንገድ፣ ለባቡር፣ ለኢነርጂ፣ ለቴኮሙኒኬሽን፣ ለመስኖ፣ ለመጠጥ ውሀና ለሳኒቴሽን መሠረተ ልማቶች ከፍተኛ ትኩረት መስጠት፣
- መንገድን በተመለከተ የዋና ዋና እና አገናኝ መንገዶች ግንባታ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በተለይ ደግሞ በሁሉም ክልሎች አዳዲስ የገጠር የመንገድ ግንባታዎችን በማካሄድ ሁሉም የገጠር ቀበሌዎች ደረጃቸውን በጠበቁና ክረምት ከበጋ በሚያገለግሉ መንገዶች ከዋና መንገድ ጋር እንዲገናኙ ይደረጋል፣

## 2.3.4 የመሠረተ ልማት ....የቀጠለ፣

- ባቡርን በተመለከተ በሶስት ኮሪደሮችና በአምስት መስመሮች አገራዊ የባቡር ኔትወርክ ግንባታዎችን በመጀመር አብዛኛዎቹን ማጠናቀቅ፤
- የሀገሪቱን የኢነርጂ ፍላጎት ለማሟላት ታዳሽ የኃይል ምንጮች በማስፋፋት ንፁህና አየርን የማይበክል ከውሀ፣ ከነፋስ፣ ከጂኦተርማል የኢነርጂ አማራጮችን የመጠቀም አቅጣጫ መከተል፣
- ቴሌኮሙኒኬሽንን በተመለከተ ወቅቱ ያፈራቸው የመገናኛ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለመሆን እንዲቻል የተጀመረውን የኔትወርክ ዝርጋታ ሰፊ ሥራ ማጠናቀቅ፣ ጥራቱ የተጠበቀ፣ ዘመናዊ፣ የተጣመሩ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን የያዘ አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ በመላ ሀገሪቱ በአፋጣኝ እንዲዳረስ ማድረግ፣

## 2.3.4 የመሠረተ ልማት ....የቀጠለ፣

- የአገሪቱ የውሀ ሀብት ለተለያዩ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት ዕንቅስቃሴዎች ዘላቂና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ መጠቀምና ማልማት፣ አጠቃላይ የመጠጥ ውሀ ሽፋንን ማሳደግ፣ የመስኖ ግንባታዎችን ማስፋፋት፣
- በከተሞች ፈጣንና ፍትሀዊ ልማትን ለማረጋገጥ ለኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ዕድገት ያላቸውን ሚና መሠረት በማድረግ መሠረተ ልማት እንዲስፋፋ ማድረግ፣ በከተሞች የሚገነቡ የመሠረተ ልማቶች ሰፊ የሥራ ዕድልና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞችን በሚፈጥር መልኩ ተፈፃሚ እንዲሆን ማድረግ፣
- የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሰው ኃይልን በብዛት የሚጠቀም፣ ልማታዊ፣ ገበያ መር፣ ጤናማ ውድድር የሰፈነበትና የግሉ ዘርፍ ከፍተኛ ሚና የሚጫወትበት፣ የሴቶችንና ወጣቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት በየደረጃው የሚያረጋግጥና የኮንስትራክሽን ዲዛይኖችም የአካል ጉዳተኞችን ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- ሳኒቴሽንን በተመለከተ ለሥራና ለመኖሪያ ተስማሚ የሆነ ንጹህ የከተማ አካባቢ እንዲኖር ማድረግ፣

## 2.3.5 የማህበራዊ ልማትን ማፋጠን እና ጥራትን ማረጋገጥ፣

### የትምህርትና ስልጠና አገልግሎት ማስፋፋትና ጥራትን ማሻሻል፣

- የተጀመረውን አበረታች ውጤት ማስቀጠል፣
- የሕፃናትን በተለይም የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ የሚገድቡ ችግሮችን ለመቅረፍ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ፣
- ለኢኮኖሚ ዕድገቱና ልማቱ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ ብቁ ዜጋ ማፍራት ቁልፍ በመሆኑ የከፍተኛ ትምህርት ጥራትን አጠናክሮ መቀጠል፣
  - በዚህ ረገድ የስልጠና ፕሮግራሙን በሳይንስና ምህንድስና መስክ ላይ ያተኮረ እንዲሆንና ጥራቱም ከሌሎች አገሮች መሰል ተቋሞች ጋር በብቃት የሚወዳደር እንዲሆን ማድረግ፣
  - የዩኒቨርስቲዎችን አስተዳደርና አመራር ስርዓትን በማሻሻል፣ ኢትዮጵያውያን ተመራማሪዎችንና መምህራንን በብዛት በማሰልጠን ጥራቱ የተጠበቀ የከፍተኛ ትምህርት ስርዓት እንዲገነባ ማድረግ፣
  - የተጀመረው የሞያና የቴክኒክ ማሰልጠኛ ተቋማት ፕሮግራም የመንግስት አቅም ግንባታ ፕሮግራም አንዱ አካል ሲሆን ፕሮግራሙ የጥቃቅንና አነስተኛ የስራ ዕድል በመፍጠር የስራ አጥነትን ለመቀነስ ጥረት ከሚያደረጉ ተቋማት ጋር በመቀናጀት መተግበር፣
  - የግል ባለሀብቶች ት/ቤቶችን እንዲከፍቱ ማበረታታት፣ ድጋፍ መስጠትና ስታንዳርዱን የጠበቀ ለመሆኑ ተገቢውን ክትትል ማድረግ፤
- ለቅድመ መደበኛና የጎልማሶች ትምህርት ትኩረት ሰጥቶ መሥራት፣
- በዘርፉ የተቀመጡ የሚሌኒየም የልማት ግቦችን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ማሳካት፣

## 2.3.5 የማህበራዊ ልማትን ማፋጠን .....የቀጠለ

### የጤና አገልግሎት ማስፋፋትና ጥራት ማሻሻልን በተመለከተ

- በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙ በመታገዝ መሠረታዊ የጤና አጠባበቅና ቁጥጥር ዙሪያ የሕብረተሰቡን የተደራጀ ተሳትፎ ማዕከል ያደረጉ ሥራዎች እንዲሠሩ ማድረግና ጥራቱ የተጠበቀ የሆስፒታል አገልግሎት መሰጠቱን ማረጋገጥ፣
- የህክምና ተቋማት በሰው ሀይልና በቁሳቁስ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት መጠናከራቸውን ማረጋገጥ፣
- በጤናው ዘርፍ የተሰማራውን የሰው ኃይል ክህሎት፣ ስብጥርና አስተዳደር ማሻሻል፣ በተለይም የህክምና ባለሙያዎች ፍልሰትን ለመቀነስ ጥረት በማድረግ ፍልሰቱንም ለማካካስ የህክምና ባለሙያዎችን የማሰልጠን ስራ በከፍተኛ መጠን እንዲያድግ ማድረግ፣
- የግሉ ዘርፍ በጤናው መስክ የሚኖረውን ሚና ይበልጥ ለማጠናከርና ለማስፋት የሚሰጡት የህክምና አገልግሎቶች ጥራታቸውን የጠበቁ ሁሉንም ወገኖች የሚያረኩ እንዲሆኑ የሌሎች አገሮችን ልምድ በመውሰድ ተገቢ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት እንዲኖር ማድረግ፣
- የመድሃኒቶችና ሌሎች የህክምና ቁሳቁሶችን ማምረቻ ተቋማት በአገሪቱ እንዲስፋፋ አስፈላጊው ማበረታቻና ማትጊያ መስጠት፣
- በዘርፉ የተቀመጡ የሚሌኒየም የልማት ግቦችን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ሙሉ በሙሉ ማሳካት፣

## 2.3.6 አቅም ግንባታንና መልካም አስተዳደርን ማሳደግ

### ➲ ግልጽነትን ማስፈን፣ ሙስናን ከምንጩ ማድረቅ

- ☞ የግብር ስርዓቱን በማሻሻልና ይህንኑ በመጠቀም የማንኛውም ዜጋ ገቢና ንብረት በወቅቱና በትክክል የሚታወቅበት ሕጋዊ እውቅናና ጥበቃ የሚያገኝበት ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት እንዲፈጠር ይደረጋል::

- ☞ የአገራችን መሬት በአጠቃላይ የከተማ መሬት በተለይ በዘመናዊ የመረጃ ስርዓት የሚመዘገብበትና የሚታወቅበት፣ በመሬቱ ላይ ማን ምን መብት እንዳለው የተሟላና ወቅታዊ መረጃ የሚኖርበትና ሕጋዊ እውቅናና ጥበቃ የሚያገኝበት ሁኔታ እንዲፈጠር በጥበቃ ክትትል ይደረጋል::

- ☞ በመረጃው ላይ በመመስረት መሬት ይበልጥ ልማታዊ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውልና በዚህ ዙሪያ የሚታዩት የኪራይ ሰብሳቢነት አዝማምያዎች እንዲከስሙ ለማድረግ ይሰራል::

- ☞ በአጠቃላይ የገቢና መሬትን ጨምሮ የንብረት መረጃ ሥርዓት መፍጠር በኢኮኖሚውና በፖለቲካው መስክ ግልፅነት ለማስፈን ብሎም ተጠያቂነት ለማስፈን ምቹ ሁኔታ ስለሚፈጥር በተሳካ ሁኔታ እንዲፈፀም ይደረጋል፣

## 2.3.6 አቅም ግንባታንና መልካም አስተዳደርን ማሳደግ...የቀጠለ

- **ጠንካራ የማስፈፀም አቅም ያለው መንግስታዊ መዋቅር መፍጠር**
  - በመተግበር ላይ ያለው የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም በሁሉም የአስተዳደር እርከኖች በተሟላ መልኩ እንዲተገበር፣ ለውጡ ስር እንዲሰድና፣ ለውጡ የአገልግሎት ቅልጥፍናን፣ የስራ ውጤታማነትን፣ ተጠያቂነትን፣ ግልፅነትን ባጣመረ አኳኋን እንዲፈፀም ለማድረግ የመንግስት ሠራተኞች የሚሰጣቸውን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል ዕውቀትና ክህሎት እንዲያገኙና ከልምዳቸውም በቀጣይነት እንዲማሩ ማድረግ፡ የሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች ህዝብን የማገልገል፣ የአገሪቱ ሕጎችና ሕገ-መንግስቱ አውቆ የማክበር፣ የመንግስት ፖሊሲዎችና እቅዶችን በተሟላ አውቆ በታማኝነት የማስፈፀም አመለካከት እንዲያዳብሩ የተቀናጀ ርብርብ ማድረግ፣
  - የፍትህ አስተዳደር ስርዓቱ የፍትህ አገልግሎት ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ የጀመራቸው ለውጦች አጠናክሮ እንዲቀጥል ድጋፍ መስጠት፣ የሚሰጡ ብይኖች ሕጉንና ሕገ-መንግስቱን መሰረት ያደረጉ፣ የሕግ የበላይነትን የሚያጠናክሩ፣ ፍትሕን የሚያሰፍኑ እንዲሆኑ ማድረግና በተለይም በሰው ኃይል ስልጠና፣ የግልፅነትና ተጠያቂነት ስርዓትን በማስፈን ረገድ ጥብቅ እንቅስቃሴ ማድረግ፣

## 2.3.6 አቅም ግንባታንና መልካም አስተዳደርን ማሳደግ...የቀጠለ

- የህዝብ ተሳትፎን ማረጋገጥ፡

  - ህዝቡ መብቱንና ግዴታውን ጠንቅቆ አውቆ ውጤታማ ተሳትፎ እንዲያደርግ፣
  - የተጠናከረ የስነ ዜጋ ትምህርት እንዲካሄድ በሕገ መንግስቱና በመሰረታዊ የአገር ግንባታ አቅጣጫዎች ላይ ሰፊ አገራዊ የጋራ አመለካከት እንዲዳብር ለማድረግ የተቀናጀ ስራ መሥራት፣
  - ህዝቡ በተለያዩ የሙያና የብዙሃን ማህበራት ተደራጅቶ መብትና ጥቅሙን ለማስከበር እንዲንቀሳቀስ አመቺ የሆነ የሕግ ማዕቀፍ በይበልጥ እንዲጠናከር ማድረግ፣
  - በመንግስት ፖሊሲዎችና ዕቅዶች አቀራረፅና አፈፃፀማቸውን በመገምገም መስክ የተደራጁ የህዝብ ማህበራትን በሰፊው የሚያሳትፍበት ስርዓት ተቀርፆ በሁሉም የአስተዳደር እርከኖች ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፣ ማህበራቱ ጠንካራ የዲሞክራሲ ማስተማሪያ መድረኮች ሆነው እንዲያገለግሉ፣ ሃሳብን በነፃ የመግለፅ ነፃነት ከመቻቻል ባህል ጋር በማጣመር፣ የሕግ የበላይነትን፣ ዜጎች መብትና ጥቅማቸውን ለማስከበር ተደራጅተውና ጠንክረው ከመንቀሳቀስ ጋር በማጣመር እንዲንቀሳቀሱ አስፈላጊውን ህጋዊ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

## 2.3.6 አቅም ግንባታንና መልካም አስተዳደርን ማሳደግ...የቀጠለ

➲ የዲሞክራሲ ተቋማትንና ባህልን ማዳበር

- ☞ የዲሞክራሲ ተቋማትን (ለምሳሌ የፌዴራልና የክልል የህዝብ ተወካዮች ም/ቤቶችን፣ የፌዴሬሽን ም/ቤትን፣ወዘተ) ከማጠናከር አኳያ ሲቪል ሰርቪስንና የህዝብ ማህበራትን ለማጠናከር የተቀመጠው አቅጣጫ በዴሞክራሲ ተቋማትም ተፈፃሚ ይሆናል፣

- ☞የህዝብ ተወካዮች ም/ኦቤቶች ሕግ የማውጣት ስልጣናቸውን በብቃት እንዲፈፅሙ አስፈላጊው የአቅም ግንባታ ስራ እንዲሰራ ይደረጋል::

- ☞አስፈፃሚውን አካል ለመከታተልና ለመቆጣጠር በየወቅቱ የተሟላና ተክክለኛ ሪፖርት እንዲቀርብላቸውና ተጨማሪ የቁጥጥር ስራዎችን ለማሳካት የተሟላ ድጋፍና ትብብር እንዲያደርጉ ይደረጋል::

- ☞የሕግ የበላይነትን ለማስፈን የሕግ አስከባሪ ተቋማት በአመለካከት፣ በቁሳቁስና በሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲጠናከሩ ይደረጋል፣

## 2.3.7 የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮች

### 1. ሴቶችንና የወጣቶችን ብቃትና ተጠቃሚነት ማሳደግ፣

- የልማት ዕቅዱ ዓላማ ሊሳካ የሚችለው ባለ ብዙ ፈርጅ የሆነው የሴቶችና የወጣቸቶች ችግር ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ ሲቀረፍና መፍትሄ ሲያገኝ በመሆኑ መንግስት የሴቶችንና የወጣቶችን ሁለንተናዊ አቅም ማሳደግና መጠቀም እንዲያስችል የሴቶች ጉዳይና የወጣቶች ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለውን አቅጣጫ አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

- በዕቅድ ዘመኑ የሴቶችንና የወጣቶችን ፓኬጅ አጠናክሮና አቀናጅቶ ተግባራዊ በማድረግ የሴቶችና ወጣቶች የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ዕድሎች እንዲሰፉና እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡

### 2. ማህበራዊ ደህንነት፣

- የሀገሪቱን ኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት በማፋጠን ሂደት ማህበራዊ ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚመለከታቸውን አካላት ያሳተፈ የማህበራዊ ደህንነት አገልግሎቶት ማስፋፋት፣ የማህበራዊ ደህንነት ችግሮችን መለየትና እርምጃዎችን መውሰድ፣ የአካልና የአዕምሮ ጉዳተኞችንና አረጋውያንን አሳታፊና ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሥራዎች ማከናወን፣

### 3. የሥነ ህዝብ ልማት

- የሥነ ህዝብ ዋና ዋና ባህሪያትን ከኢኮኖሚ አቅም ጋር ለማጣጣም የሚያስችሉ ጠንካራ መሠረቶች መፍጠር፣

## 2.3.7 የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮች....የቀጠለ

### 4. ኤች አይ ቪ /ኤድስ

- ህብረተሰቡን ማዕከል ያደረገና በኤች አይ ቪ ኤድስ ፕሮግራም ላይ የተመሰረተ በብሔራዊ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፖሊሲና በፀረ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፓሊሲ መድኃኒት አጠቃቀምና አቅርቦት ስልት ላይ የተመሠረተ የባለብዙ ዘርፍ (Multi Sectoral) የኤች አይ ቪ ኤድስ የጤና አገልግሎት ፕሮግራም ተጠናክሮ ተፈፃሚ እንዲሆን ማድረግ፣

### 5. ባህልና ቱሪዝም

- የባህል ኢንዱስትሪን በማሳደግና በማስፋፋት ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ድርሻ እንዲኖረው ማድረግ፣ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ተወዳዳሪ ሆኖ በተለይ በአፍሪካ ተመራጭ መዳረሻ እንዲሆንና የሕዝብ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ የአገሪቱን መልካም ገጽታ መገንባት፣

### 6. የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮች

- በኢኮኖሚ ዕድገትና ማህበራዊ ልማት ላይ ተፅዕኖ የማያስከትል አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት በሥራ ላይ ያሉ የአካባቢ ህጎችንና የአካባቢ እንክብካቤ ሥርዓቶችን የመተግበርና በተለይም አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት የሚካሄደውን አገራዊ ጥረት ለማሳካት የሚያስችል አቅም መገንባት፣

## 2.4 የማክሮ ኢኮኖሚና የዋና ዋና ዘርፎች ግቦች

ከፍ ብሎ የተቀመጡትን የአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዋና ዋና ዓለማዎች መሠረታዊ አቅጣጫዎችን በመከተል ተፈፃሚና ስኬታማ ለማድረግ የማክሮ ኢኮኖሚ እና የዋና ዋና ዘርፎች ግቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

# ሠንጠረዥ 2.4.1 የማክሮ ኢኮኖሚ እና የዋና ዋና ዘርፎች ግቦች

| ዘርፍ/አመልካች | መነሻ (2002) | መድረሻ (2007) |
|---|---|---|
| **ሀ. የማክሮ ኢኮኖሚ ግቦች** | | |
| ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ዕድገት (Real) (በመቶኛ) | **10.4** | **11.4** |
| የነፍስ ወከፍ ገቢ በጊዜው የገበያ ዋጋ (በአሜሪካን ዶላር) | **377** | **482/523** |
| ጠቅላላ የፍጆታ ወጪ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በመቶኛ | **94.5** | **85.0** |
| ጠ/የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንት ከጠ/የአገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በመቶኛ | **22.3** | **28.2** |
| ጠቅላላ የወጪ ንግድ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በመቶኛ | **13.6** | **22.5** |
| ጠቅላላ የገቢ ንግድ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በመቶኛ | **33.0** | **35.7** |
| የሀብት ክፍተት ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በመቶኛ | **(19.3)** | **(13.1)** |
| ጠቅላላ የአገር ውስጥ ቁጠባ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በመቶኛ | **5.5** | **15.0** |
| የአገር ውስጥ ገቢ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በመቶኛ | **14.0** | **17.1** |
| የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በመቶኛ | **11.3** | **15.0** |
| አጠቃላይ የድህነት ተኮር ወጪ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በመቶኛ | **12.3** | **17.3** |
| የካፒታል ወጪ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ (በመቶኛ) | **10.3** | **14.4** |
| የመደበኛ ወጪ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ (በመቶኛ) | **8.4** | **9.3** |
| ከአጠቃላይ ድህነት መሥመር በታች የሚኖረው ሕዝብ ብዛት በመቶኛ | **29.2** (ግምት) | **22.2** |
| ከምግብ ድህነት መስመር በታች የሚኖር ሕዝብ ብዛት በመቶኛ | **28.2** (ግምት) | **21.2** |

## ሠንጠረዥ 2.4.1 ….የቀጠለ

| ዘርፍ/አመልካች | መነሻ (2002) | መድረሻ (2007) |
|---|---|---|
| **ለ. የኢኮኖሚ ልማት ግቦች** | | |
| **1.ግብርና** | | |
| የግብርና ዕድገት በመቶኛ | 7.6 | 8.7 |
| የግብርና ምርታማነት (ኩንታል/ሄክታር) | 17.0 | 22.0 |
| የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎች ብዛት በሺህ ቁጥር | 5090 | 14640 |
| የአበባ ምርት በሚሊዮን ዘንግ | 2748.0 | 5859.1 |
| በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የሚሳተፉ ቤተስቦች ቁጥር በሚሊዮን | 7.1 | 1.3 |
| **2. ኢንዱስትሪ** | | |
| የስኳር ምርት መጠን በሺህ ቶን | 314.5 | 2250 |
| የስኳር ምርት ኤክስፖርት በሚሊዮን ቶን | - | 1.246 |
| የስኳር ኤክስፖርት ገቢ በሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር | | 661.7 |
| የጨርቃጨርቅና ስፌት ኢንዱስትሪ ኤክስፖርት ገቢ በሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር | 21.8 | 1000 |
| የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ኤክስፖርት ገቢ በሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር | 75.73 | 496.5 |
| የአገሪቱን አጠቃላይ ሲሚንቶ የማምረት አቅም በሚሊዮን ቶን | 2.7 | 27 |
| የብረት ብረት የነፍስ ወከፍ ፍጆታ በኪ.ግ. | 12 | 34.72 |

## ሠንጠረዥ 2.4.1 ….የቀጠለ

| ዘርፍ/አመልካች | መነሻ (2002) | መድረሻ (2007) |
|---|---|---|
| **3. ማዕድን** | | |
| የወርቅ ኤክስፖርት በኪሎ ግራም | **3907** | **8700** |
| በባህላዊ ማዕድናት አምራቾች ለብሔራዊ ባንክ የቀረበ የወርቅ መጠን በኪ.ግ. | **2866** | **5250** |
| **4. መንገድ** | | |
| አጠቃላይ የመንገድ ርዝመት (በሺህ ኪ.ሜ) | **48.8** | **64.5** |
| ለሁሉም አየር ፀባይ ከሚሆን መንገድ ለመድረስ የሚወስደው ጊዜ በሰዓት | **3.7** | **1.4** |
| የመንገድ ጥግግት (ኪ.ሜ/1000 ኪ.ሜ ስኩዌር) | **44.5** | **123.7** |
| የመንገድ ጥግግት (ኪ.ሜ/1000 ህዝብ አሰፋፈር) | **0.64** | **1.54** |
| በጥሩ ይዞታ ላይ የሚገኝ መንገድ (በመቶኛ) | **81** | **86.7** |
| ለሁሉም የአየር ፀባይ ከሚሆን መንገድ በ5 ኪ.ሜ ርቀት በላይ የሚገኙ ቦታዎች (በመቶኛ) | 64 | **29** |
| ለሁሉም የገጠር ቀበሌዎች ደረጃውን በጠበቀና ክረምት ከበጋ የሚያገለግል እና ከዋና መንገድ ጋር የሚያገናኝ አዲስና ጥገና የሚደረግለት የገጠር የመንገድ ግንባታ (ኪ.ሜ.) | **0** | **71523** |

## ሠንጠረዥ 2.4.1 .....የቀጠለ

| ዘርፍ/አመልካች | መነሻ (2002) | መድረሻ (2007) |
|---|---|---|
| **5. ባቡር** | | |
| የባቡር ትራንስፖርት ኔትወርክ (በኪ.ሜ.) | **0** | **2395** |
| **6. ኢነርጂ** | | |
| የመብራት አገልግሎት ሽፋን (በመቶኛ) | **41** | **75** |
| የኃይል ማመንጨት አቅም (ሜጋ ዋት) | **2000** | **8000** |
| የኃይል ማሰራጫ የኃይል ብክነትን መቀነስ ( በመቶኛ) | **11.5** | **5.6** |
| አዳዲስ የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት የሚያገኙ ደንበኞች (በቁጥር) | **2000000** | **4000000** |
| የማከፋፈያ መስመር ግንባታ (ርዝመት በኪ.ሜ.) | **126038** | **258038** |
| የኃይል ማሰራጫ መስመር መልሶ ግንባታ (ርዝ መት በኪ.ሜ) | **450** | **8130** |
| **7. ቴሌኮሙኒኬሽን** | | |
| የቴሌፎን አገልግሎት ሽፋን በ5 ኪ.ሜ ርቀት ውስጥ (በመቶኛ) | **62.14** | **100** |
| የሞባይል ስልክ ሥርጭት (በመቶኛ) | **8.7** | **45.0** |
| የመበደበኛ ስልክ ተጠቃሚዎች (በሚሊዮን) | **1.00** | **3.05** |
| የሞባይል ስልክ ተጠቃሚዎች (በሚሊዮን) | **6.52** | **40** |
| የኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች (በሚሊዮን) | **0.187** | **7.17** |

## ሠንጠረዥ 2.4.1 .....የቀጠለ

| ዘርፍ/አመልካች | መነሻ (2002) | መድረሻ (2007) |
|---|---|---|
| **8. ውሀ** | | |
| አጠቃላይ መጠጥ ውሃ ሽፋን በመቶኛ | 68.5 | 98.5 |
| ንፁህ መጠጥ ውሃ ሽፋን በከተማ (0.5 ከ.ሜ ክልል ውስጥ) በመቶኛ | 91.5 | 100 |
| የንፁህ መጠጥ ውሃ ሽፋን በገጠር (በ1.5 ኪ.ሜ ክልል ውስጥ) | 65.8 | 98 |
| በመካከለኛና በከፍተኛ መስኖ የለማ መሬት በመቶኛ | 2.5 | 15.6 |
| **9. ኮንስትራክሽንና ከተማ ልማት** | | |
| የከተማ ሥራ አጥነትን ለመቀነስ በቤቶች ልማት ፕሮግራም አማካኝነት የተፈጠሩ የስራ ዕድሎች በሺህ ቁጥር | 176 | 370 |
| በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት አማካኝነት የተፈጠረ የሥራ ዕድል በሚሊዮን ቁጥር | - | 3 |
| መጠለያና መሰረታዊ አገልግሎት ማቅረብ በቤቶች ቁጥር | 213000 | 700000 |
| የተጎዱና የተጨናነቁ አከባቢዎችን መቀነስ በመቶኛ | 60 | 30 |
| በከተሞች የድንጋይ ንጣፍ መንገድ ግንባታ በኪ.ሜ | - | 3648 |
| በቤት ልማት ፕሮግራሙ የሚቋቋሙ ኢንተርፕራይዞች ብዛት በቁጥር | | 5000 |

## ሠንጠረዥ 2.4.1 .....የቀጠለ

| ዘርፍ/አመልካች | መነሻ (2002) | መድረሻ (2007) |
|---|---|---|
| **መ. ማህበራዊ ልማት** | | |
| **1. የትምህርት** | | |
| የአንደኛ ደረጃ ንጥር ተሳትፎ በመቶኛ | 87.9 | 100 |
| የሥርዓተ ፆታ የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ ጥምርታ | 0.93 | 1.0 |
| የተማሪ መጽሐፍት ጥምርታ | 1.25:1 | 1:1 |
| የጎልማሶች ትምህርት ተሳትፎ በመቶኛ | 36 | 95 |
| የመንግስት ከፍተኛ ተቋማት የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ጠቅላላ ብዛት በቁጥር | 185788 | 467000 |
| የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ተማሪዎች ጠቅላላ ብዛት በቁጥር | 430562 | 1127330 |
| **2. ጤና** | | |
| የጤና አገልግሎት ሽፋን (በመቶኛ) | 89 | 100 |
| ከአምስት ዓመት በታች ያሉ ህፃናት ሞት መጣኔ ከ1000 | 101 | 68 |
| የእናቶች ሞት መጣኔ ከ100000 | 590 | 267 |
| የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ተጠቃሚዎች (በመቶኛ) | 32 | 66 |
| በሰለጠነ የጤና ባለሙያ የታገዙ ወላዶች መጣኔ በመቶኛ | 25 | 60 |

# ሠንጠረዥ 2.4.1 .....የቀጠለ

| ዘርፍ/አመልካች | መነሻ (2002) | መድረሻ (2007) |
|---|---|---|
| **ሐ. ማህበራዊ ልማት** | | |
| **2. ጤና......የቀጠለ** | | |
| የወባ መከላከያ አጎበር ተጠቃሚ የሆኑ የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች በመቶኛ | 100 | 100 |
| በኤች አይ.ቪ. ኤድስ አዲስ አዲስ የሚያዙ ሰዎች ብዛት በመቶኛ | 0.28 | 0.14 |
| **ሠ. የሥርዓተ ፆታ ልማት** | | |
| **1. የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ማሳደግ** | | |
| የሴቶችን ውሳኔ ሰጪነት (በፓርላማ) ማሳደግ በመቶኛ | 29 | 35 |
| የሴቶችን ውሳኔ ሰጪነት (በህግ ተርጓሚ) ማሳደግ በመቶኛ | 19.8 | 25 |
| የሴቶችን ውሳኔ ሰጪነት (በአስፈፃሚ) ማሳደግ በመቶኛ | 19.4 | 25 |
| **2. በሴቶች ላይ የሚደረጉ ጥቃቶችን መቀነስ በመቶኛ** | | |
| • ግርዛትን መቀነስ | 37.7 | 0.7 |
| • ያለዕድሜ ጋብቻን መቀነስ | 21.4 | 10.4 |
| • ጠለፋን መቀነስ | 12.7 | 0.2 |

## 2.5 የአቅም ግንባታና መልካም አስተዳደር ግቦች

**ሀ. የአቅም ግንባታን በተመለከተ**

- የበላይ አመራር ብቃትን ማሳደግ፣
- የሰው ኃብት (የለውጥ ሰራዊት) ብቃትን ማጐልበት፣
- የመንግስት ተቋማትን ብቃት ማሳደግ፣
- ውጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ግልጽና ተጠያቂ የመንግስት የፋይናንስ ስርዓትን ማስፈን፣
- የአቅም መገንቢያ ተቋማትን አቅም ማሳደግ፣
- የለውጥ ኮሙኒኬሽንን ማጐልበት፣
- የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራርን ማሳደግ፣
- ኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባርን መቀነስ፣
- የህብረተሰብ ተሳትፎን ማሳደግ፣

**ለ. የፍትህ ሥርዓት ማሻሻልን በተመለከተ**

- የሰው ሀይል ብቃትን ማጎልበት፣
- የፍትህ ስርዓቱን የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር ማሻሻል፣
- የዳኝነት ነጻነት፣ ግልጽነት ተጠያቂነት ማረጋገጥ፣
- የአገልግሎት ተደራሽነትን ማጎልበት፣
- ታራሚዎችን ማነጽ፣

**ሐ. የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን ማጠናከርን በተመለከተ**

- የዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ተቋማትን ማጠናከር፣
- አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረተሰብ መፍጠር፣
- የህዝቡን ተሳትፎ ማረጋገጥ፣

**መ. መልካም አስተዳደር ማስፈንን በተመለከተ**

- ምንጩ ያልታወቀ እና ሕጋዊ ያልሆነ ሀብት ከተገኘ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፣
- ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት ከምንጩ ለማድረቅ የተጠናከረ የሥነ ምግባር እና የፀረሙስና ትምህርቶችን በማስፋፋት የነቃ እና ሙስናን ሊሸከም የማይችል ሕብረተሰብ መፍጠር፣

## 2.6 የዕቅድ አፈፃጸም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት

- በዕቅዱ የትግበራ ሂደት በማክሮና በዋና ዋና ዘርፎች ወደ ተቀመጡ ግቦች እየተደረሰ ስለመሆኑ የሚታወቅበት ግልፅና የተሟላ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡
- የክትትልና ግምገማ ሥርዓቱ በዕቅዱ አፈፀጸም ዙሪያ የተሟሉና ወቅታዊ መረጃዎችን ይጠይቃል፡፡ እነዚህ መረጃዎች በአገሪቱ የተለያዩ የአስተዳደር ዕርከኖች ቁልፍ የልማት ሚና ከሚጫወቱ የልማት ኃይሎች (ከመንግስት፣ ከግሉ ዘርፍ ባለሀብቶች፣ ከህዝቡ) የሚገኙ ናቸው፡፡
- የዕቅዱ የአፈፃጸም ክትትልና ግምገማ መረጃዎች በማያቋርጥ ምዝገባ እየተሰበሰቡ በአስተዳደር መዛግብት በተሟላ ሁኔታ በየዘርፉ መያዝ እና ከወረዳ እስከ ክልል እና ፌዴራል ዘርፍን መሠረት በማድረግ እንደሚፈሱ ይጠበቃል፡ እነዚህን መረጃዎች መሠረት በማድረግ የኢኮኖሚውን አፈፃጸም አገራዊ ሥዕል የሚያሳዩ ወቅታዊ የፈጻጸም ሪፖርቶች በዘርፍና በማክሮ ደረጃዎች ተዘጋጅተው ለሚመለከታቸው አካላት እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡
- እንደዚሁም በቆጠራና በናሙና ጥናት የኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ የዲሞግራፊያዊና የስነ-ምድር የስታቲስቲካዊ መረጃዎች እየተሰበሰቡ በተቀናጀ አሠራር ተቀነባብረውና ተተንትነው ለተጠቃሚዎች ይሰራጫሉ፡፡
- የክትትልና ግምገማ ሥራውን ውጤታማና ስኬታማ ለማድረግ እያንዳንዱ ዜጋ፣ የመንግስት አካላት፣ የግል ባለሀብቶች... በአጠቃላይ የልማት ኃይሎች ጉዳዩ የራሳቸውና የአገራቸው መሆኑን ተገንዝበው የዕቅዱን አፈፃጸም በባለቤትነት መከታተልና የሚጠየቁ ትክክለኛ መረጃዎችን በወቅቱ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 2.7 ማጠቃለያ

- የአምስት ዓመቱ የእድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በመሠረታዊ እና በከፍተኛ የዕድገት አማራጮች የተዘጋጀ ነው፡፡ ከፍተኛው የዕድገት አማራጭ የግብርና ምርትን እና አጠቃላይ ኢኮኖሚውን በ2002 ከነበሩበት በ2007 ዕጥፍ የሚያደረግ ነው፡፡ ይህ የዕድገት ግብ ሁሉም የአገሪቱ ዜጎች በየደረጃው ድርሻቸውን ከተወጡ እንደሚሳካ አያጠራጥርም፡፡ ስለሆነም፡-
    - ይህንን የዕድገት ግብ ለማሳካት ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ይጠይቃል፣
    - ዕድገቱ የሚጠይቀውን ከፍተኛ ኢንቨስትምንት ዕውን ለማድረግ ከፍተኛ የአገር ውስጥ ቁጠባ ያስፈልጋል፣
    - መንግሥት የህበረተሰቡን የታክስ ግንዛቤ በማስፋት የታክስ ገቢን ትርጉም ባለው ሁኔታ ማሳደግ፣ ከኢንቨስትመንት ጋር ያልተያያዙ ወጭዎችን በቁጠባና በማብቃቃት በመጠቀም ኢንቨስትመንትን ማሳፋፋት፣
    - የግሉ ዘርፍ፣ ግለሰቦች፣ ቤተሰቦች፣ የሕ/ሥራ ማሕበራት...ወዘተ የቁጠባ ባሕላቸውን እንዲያሳድጉና እንዲያዳብሩ በማበረታታት የአገር ውስጥ ቁጠባን ማሳደግ፣
    - የግሉ ዘርፍ የኢኮኖሚ ተዋናዮችም የቆጠቡትን መዋዕለ ንዋይ በልማት ሥራ ላይ እንዲያውሉ (በኢንቨስትመንት ሥራ ላይ እንዲያውሉ) ማበረታታትና ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣

## 2.7 ማጠቃለያ....የቀጠለ

- በአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በመመራት በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ኢንዱስትሪው በኢኮኖሚው ውስጥ የመሪነት ሚናውን ለመረከብ ዝግጅቶች የሚጠናቀቁበት ይሆናል፡፡

- በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ግዙፍ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ይካሄዳሉ፡፡ የሚገነቡት መሠረተ ልማቶች ለኢኮኖሚው ፈጣን ዕድገትና ማህበራዊ ልማት ዘላቂነት አስተማማኝ መሠረት ከመሆናቸው በተጨማሪ ገቢን በማመንጨትና የውጭ ምንዛሬን በማዳን ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፡፡

- በአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ዘመን መጨረሻ አገራችን በተቀናጀና በተባበረ ልማታዊ ክንድ የሚሌኒየሙን የልማት ግቦች ሙሉ በሙሉ ታሳካለች፡፡

## 2.7 ማጠቃለያ....የቀጠለ

- የልማት ዕቅዱ በትግበራ ላይ በሚውልባቸው የሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የተጀመሩ የአቅም ግንባታ ሥራዎች በተለያዩ የአስተዳደር ዕርከኖች ተጠናክረው የሚቀጥሉ ሲሆን መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ግልፅነትንና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጡ ሥራዎች ከምንጊዜውም በላቀ ሁኔታ በትኩረት ይሠራሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የፍትህ ሥርዓቱ የበለጠ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆንና ዴሞክራታይዜሽን ስፋትና ጥልቀት በአለው ሁኔታ እንዲሰርፅ ይደረጋል፡፡

- የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን ለማሳካት እንደዜጋ፣ እንደባለሙያ፣ እንደባለሀብት፣ እንደ አመራር፣ እንደህዝብ፣ እንደ አገር መሠረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ማድረግ ይጠበቃል፡፡ ስለሆነም ለለውጥ፣ ለዕድገትና ለልማት እንቅፋት የሆኑ አስተሳስቦችን እና የጥገኝነት አመለካከቶችን በማስወገድ በተጨባጭ ሊታዩና በተግባር ሊረጋገጡ ወደሚችሉ ልማታዊ አስተሳሰቦች ሽግግር በከፍተኛ ትኩረትና ርብርብ እንዲከናወን ይደረጋል፡፡ ይህ በገንዘብ የማይለካ ከፍተኛ የልማት ኃይል ነው፡፡

- የእነዚህ ሁሉ ድምር ውጤት አገራችንን በ2012-2015 መካከለኛ ገቢ ካላቸው ተርታ ለማሰለፍና በተቀናጀና በተባበረ የጋራ ጥረት ድህነትን ተረት ለማድረግ የተጀመራውን ህዳሴ ያሳካል፡፡